# ሜይ ዴይ የትግል ቃል ኪዳናችን ቀን ነው !

## በስደት ከሚገኙ የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማሕበራት መሪዎች ለሜይ ዴይ 2001 የተሰጠ መግለጫ !

የኢትዮጵያ ሰራተኞች ዘንድሮም ዓለም አቀፍ የሰራተኞች ቀን ሜይ ዴይን ከዓለም ሰራተኞች ጋር ያከብሩታል:: የሜይ ዴይ አከባበር በየሃገሩ የተተከሉት ሥርዓቶችን ምንነት በሚያሳይም ሁኔታ ነው የሚከበረው።

የኢትዮጵያ ሠራተኛ ሕዝብ የዘንድሮ ሜይ ዴይንም የሚያከብረው እንደቀደሙት የሜይ ዴይ በዓላት ሁሉ መደባዊ መብቱ በወያኔ አገዛዝ ተገፎ፣ ሰባዊ ክብሩ ተዋርዶ፣ሰርቶ የማደር መብቱ ባልተጠበቀበት፣ እየሰራ በሚራብበት ፣ እሱና ቤተሰቡ የበይ ተመልካች ሆነው ጥቂት የገዥው ቡድን አባላት በሱ ላብ በድሎት በሚሞላቀቁበት፣ የሱ ልጆች ደብተር እና እርሳስ እያረረባቸው የገዥው ቡድን ልጆች በሱ ላብ በውጭ ሃገራት ውድ ትምሕርት ቤቶች በሚንደላቀቁበት፣ የግፍ እና የሰቆቃ ሁኔታ ውስጥ ነው።

ላብ አደሩ እንዲህ የአምባገነኖች የግፍ ጽዋ ሞልቶ ሲፈስ በሕግ አምላክ የሚልበትን ማሕበሩን ጭምር በጠመንጃ ተነጥቆ መጠለያ ያጣበት ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ነው የዘንድሮ ሜይ ዴይንም የሚያከብረው። የሰራተኛ ማሕበራቱን አመራር የተቆጣጠሩት ላብ አደሩ በነጻነት የመረጣቸው መሪዎች ሳይሆኑ በወያኔ ድርጅታዊ ሥራ የተሾሙ ሆድ አደር ግለ-ሰቦች በመሆናቸው ሠራተኛው መብቱን ለማስጠበቅ የሚያደርገውን ትግል የሚያስተባብሩና መርተው ለውጤት የሚያበቁ ሣይሆኑ የሰራተኛውን የሙብት ጥያቄ ለማፈን የሚሩዋሩዋጡ የወያኔ ቅጥረኛ ተላላኪዎች ናቸው።

በላብ አደሩ ማሕበራት ላይ ወያኔ የጫናቸው ሆድ አደሮች ዋና ተልኮ የላብ አደሩን መብት ለማስከበር መታገልና ማታገል ሳይሆን ላብ አደሩ ለወያኔ ጸረ ሕዝብ አገዛዝ ሰጥ ለጥ ብሎ እንዲገዛና እንዲያጎበድድ ማዋከብና ማስፈራርት ነው።

የአምባ ገነን እና ግፈኛ አገዛዝ ዕድሜ የሚረዝመው አለመተማመን እና ፍርሐት በሕዝብ ላይ ሲሰፍን በመሆኑ በሰራተኛው ማሕበራት ላይ ከኮንፌዴሬሽን እስከ መሰረታዊ ማሕበራት የተተከሉት የወያኔ ካድሬዎች ከወያኔ የተረከቡት አቢይ አደራ ሠራተኛውን ሕዝብ መሰለል ማዋከብና ማስፈራራት፣ እንዲሁም እርስ በርሱ እንዳይተማመን ከፋፋይና በታኝ ሴራዎችን መፈብረክ ነው።

እነዚህ ወይኔ በሰራተኛው ማሕበራት ላይ የበተናቸው በሆድ የተገዙ ግሪሳዎች የሰራተኛ ማሕበራትን ከማኮላሸት፣ ሠራተኛውን ከማዋከብና ከማስፈራራት በተጨማሪ የሃገሪቱ ኤኮኖሚ ወያኔ ባቁዋቁዋማቸው የዘረፋ ተቁዋማት አማካኝነት በወያኔ ቁጥጥር ሥር እንዲገባ ተወዳዳሪ የሆኑና ለወያኔ ያላጎበደዱ የግል ባለሃብቶችንም የማዳከም ሥውር ተልኮ ጭምር ይዘው መቆየታቸው የአደባባይ ምስጢር ነው።

እነዚህ ሆዳቸውን ለሞላላቸው ወያኔ በሎሌነት አድረው ሠራተኛውን ሕዝብ ሲሰልሉ እና ሲያዋክቡ የሚውሉ የወያኔ ተላላኪዎች ሜይ ዴይ በመጣ ቁጥር ከዚህ በውርደት ከነተበ ማንነታቸው አኩዋያ ማጋለጥ የግድ ነው። ታሪክም ፍርዳቸውን አይነፍጋቸውም።

EthioLion.Com

ላብ አደሩ የራሱን መብት እና ነጻነት ከሀገሩ መጻኢ ዕድል ነጥሎ አይመለከትም። በመሆኑም ከመደባዊ ትግሉ ጎን ለጎን ወያኔ የሃገሪቱን ሀብት በብቸኝነት ተቆጣጥሮ ሀገሪቱን የአንድ ጠባብ እና ዘረኛ ቡድን ጥገት ለማድረግ የሚደርገውንም ሩጫ በንቃት መከላለልና ማጋለጥ የዜግነት ግዴታው መሆኑን ተረድቶ በተለያዩ ቦታዎች እያሳየ ያለውን የሃገር ኤኮኖሚ የመጠበቅ ትንቅንቅ አጠናክሮ ሊቀጥል የግድ ነው።

የኢትዮጵያ ላብ አደር ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን ቆሞ ባካሄደው ትግል አረመኔው የወያኔ ሥርዓት የቆመባት ምድር ከለት ወደ ዕለት እየከዳችው ነው። እራሱ ያወጣቸውን ሕጎች ጭምር እየጨፈላለቀ በሁሉም የሕብረተሰብ ክፍሎች ላይ አፈናውን እና ጭፍጨፋውን ቢያጠናክርም፣ የየዕለቱ ክስተት የሚያረጋግጠው ሃቅ ይህ ሁሉ አፈና ወያኔ ወደ መቃብሩ የሚያደርገውን ጉዞ ከማፍጠን የተለየ ውጤት ያልሰጠ መሆኑን ነው።

የወያኔ ሥርዓት የሚይዘውን እና የሚጨብጠውን አጥቶ ሁሉንም እንደ አበደ ውሻ እየተናከሰ ነው። የራሱ የፕሮፓጋንዳ መሳሪያዎችም በየዕለቱ የሚያረጋግጡልን ይህንኑ ነው። ከዚህ ቀበሌ ገበሬ ማሕበር ይህን ያሕል ወንበዴ ማረኩ፣ ነጋዴዎች የኤኮኖሚ አሻጥር ሲፈጽሙ በቁጥጥር ሥር አዋልኩ፣ ወታደሮች እና ሲቭሎች ተመሳጥረው መፈንቅለ መንግሥት ሊያደርጉብኝ ሲሉ ደረስኩባቸው እያለ በራሱ ሚዲያዎች ቀን ከሌት የሚያሰማቸው ኡኡታዎች ሁሉ የሚያረጋግጡት ሃቅ ቢኖር ወያኔ በሁሉም ሕብረተሰብ ክፍሎች ተተፍቶ በሕዝባዊ ቁጣ ወደ መቃብሩ የሚወርድበት ጊዜ የተቃረበ መሆኑን ነው።

የኢትዮጵያ ላብ አደር ቀደምት ፋና ወጊ መሪዎቹ እነ አበራ ገሙ እና እነ ዳሮ ነጋሽ ለሰራተኛው መብት ሲሉ ልጆቻቸውን በትነው የከፈሉትን የሕይወት መሥዋዕትነት በሜይ ዴይ ሲዘክር ይሕን የተቀጣጠለ ሕዝባዊ ትግል ዛሬም እንደትላንቱ ከሕዝብ ጎን ቆሞ ከግብ ለማድረስ የትግል ቃል ኪዳኑን በማደስ ነው።

እነ አበራ ገሙ በለኮሱት የትግል ችቦ ውጋጋን እየተመራ የውያኔን ድቅድቅ ጨለማ መሰንጠቅ የጀመረው ትግል በአንጋፋው የምድር ባቡር ላብ አደሮች የ እምቢ ለመብቴ ትግል ዘንድሮም ጎልቶ ታይትዋል። በየዕርከኑ እየታዩ ያሉት ተመሳሳይ የመብት ማስከበር ትንቅንቆች ተጠናክረው የወያኔ የግፍ ሥርዓት ተሰባብሮ እስኪወድቅ ይቀጥላሉ። እነዚህ በየቦታው እየታዩ ያሉት የላብ አደሩ የመብት ጥያቄዎች ተራ በተራ በወያኔ እየተመቱ እንዳይኮላሹ የአንዱ ዘርፍ ላብ አደሮች ያነሱትን ጥያቄ ሁሉም በሕቡዕና በግልጽ እየደገፈና እያጠናከረ ትግሉ በተናጠል እንዳይታፈን እና እንዳይመታ ቢጋራ ሊመክት ይገባዋል።

ይህ በመቃብሩ አፋፍ ላይ ቆሞ የሚያቅራራ የወያኔ የግፍ ሥርዓት ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሚወገድበትና የኢትዮጵያ ላብ አደርና መላው ሕዝብ የዕውነተኛ መብት እና ነጻነት ባለቤት የሚሆንበትን ጊዜ ለማቅረብ ሃቀኛ ላብ አደሮች ዛሬም እንደትላንቱ በትግሉ ግንባር ለተሰለፉት ጸረ ወያኔ ሀይሎች እንደ አመችነቱ በሕቡዕም ሆነ በግልጽ ድጋፋቸውን በመስጠት ታሪካዊ አደራቸውን ይወጣሉ።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !

ነጻነት ምን ጊዜም የመስዋዕትነት ውጤት ነው !

በስደት ከሚገኙ የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማሕበራት መሪዎች ለሜይ ዴይ የተሰጠ መግለጫ !

እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ሚያዝያ 2001

EthioLion.com